ከ ጆርጅ አንደርሰን

# የፌደራለዊ መንግስት አወቃቀር መነሻ ነጥቦች

በሚል ርዕስ ከተፃፈ መጽሃፍ የተወሰደ

መጋቢት 2001 አዲሰ አበባ - አትዮጵያ

# አንድነትና ብዙሀነት

## የአንድነት ፈተናዎች

በብዙ ፌዴሬሽኖች፤ በተለይም የመደብ፣ የቋንቋ፣ የብሔረሰብ፣ የሃይማኖትና ሌሎች ልዩነቶች ከፍተኛ ክፍፍል ሲኖር፤ የአንድነት ጥያቄ ቁልፍ አጀንዳ ወይም ፈተና ነው፡፡ ከፍተኛ የአንድነት ፈተና፤ በፌዴራላዊ ወይም ፌዴራላዊ ባልሆኑ ስርአቶች ውስጥ ሊኖር ይችላል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ፤ ፈተናው የመገንጠል ንቅናቄን መልክ ይይዛል፡፡

ፌዴሬሽኖች፤ በተቋሞቻቸውና በማህበራዊ ጥንቅራቸው እጅግ የተለያዩ መሆናቸውን አይተናል፡፡

- አንዳንዶቹ፤ አንፃራዊ ወጥነት አላቸው፤ ዜጎች ጠንካራና ገናና የአገራዊ ማንነት ስሜት ይጋራሉ፡፡ በእነዚህ ፌዴሬሽኖች ውስጥ፤ አንድነት ከፍተኛ አጀንዳ አይደለም፤ በፌደሬሽኑ ውስጥ ያሉት ማህበራዊ ኃይሎችም፤ ብዙውን ጊዜ ይበልጥ ማዕከላዊነትን ለማጠናከር ግፊት ይፈጥራሉ፡፡
- ሌሎች ፌዴሬሽኖች በእጅጉ ብዙሀነት ይታይባቸዋል፡፡ ዜጎች፤ ተቃራኒ አመለካከቶችና ዓላማዎችን ከሚያንፀባርቁ የተለያዩ ቡድኖች ጋር ራሳቸውን ይፈርጃሉ፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ የአንድ ቡድን ወይም የአንድ ህዝብ አባላት፤ የራሳቸው ማንነት ከአገራዊው ማንነት ጋር የማይጣጣም አድርገው ሊመለከቱ ይችላሉ፤ ስለሆነም በአገራዊ ማንነት ጉዳይ ዙሪያ ውጥረትን ይፈጥራሉ - በተለይ ክልላዊ የአሰፋፈር ክምችት ሲኖራቸው፡፡

በ19ኛው ክፍለ ዘመን፣ ብሪታኒያ ውስጥ የአየርላንድ የራስ አስተዳደር ንቅናቄ፣ ረጅሙ የደቡብ ሱዳን የእርስበርስ ጦርነት፣ በስፔን በፍራንኮ አገዛዝ ዘመን የባስክ አመፅ፣ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ስሪላንካ ውስጥ የታሚል አማፂዎች፣... እነዚሁ ሁሉ በአሃዳዊ አገሮች ውስጥ ካጋጠሙ የአንድነት ከባድ ፈተና ምሳሌዎች ናቸው፡፡ አሜሪካ፣ ናይጀሪያና ፓኪስታን፣ በእርስበርስ ጦርነት ዘመኖቻቸው፣ እንዲሁም በኩቤክ የመገንጠል ንቅናቄ የተጋረጠባት ካናዳ፣... እነዚህ ደግሞ፣ የአንድነት ፈተናዎች የተጋረጡባቸው ፌዴሬሽኖች ምሳሌ ናቸው፡፡ የመገንጠል ንቅናቄ አደጋ፣ ብዙ ጊዜ ከፌዴራሊዝም ጋር ተያይዞ የሚነሳ ቢሆንም፣ በታሪክ እንደታየው የመገንጠል ንቅናቄ በበርካታ አሃዳዊ አገሮች በብዛት ሲከሰት ቆይቷል፡፡

## ብዙሀነትን ማፈን

ከፍተኛ የአንድነት ፈተናዎችን፣ በአፈና፣ በማግለልና በማካተት ፖሊሲዎች መመለስ ይቻላል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ብዙ ጊዜ ችግሩን ያባብሳሉ፣ ወደ ግጭት የሚመራ አደጋም ይጋብዛሉ፡፡

አንዳንድ መንግስታት፣ በተለይም ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑት አገራት ውስጥ፣ የተለያዩ የህዝብ ክፍሎችን፣ በስፋት ወደሚታየው የአኗኗር ዘይቤ እንዲካተቱ በመሞከር፣ ወይም ፖለቲካዊ ነፃነቶቻቸውን በማፈን በአንድነት ላይ ለሚፈጠሩ ፈተናዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ከታሪክ አንፃር፣ ሲታይ አናሳዎችን ወደ ሰፊው ህዝብ በማቀላቀል በኩል ለምሣሌ፣ የብዙሃኑን ህዝብ ቋንቋ እንዲይዙ በማድረግ በኩል አንዳንድ የማካተት ፖሊሲዎች ቢሳካላቸውም፣ ጠንካራ ብሶትና የመነጠል ስሜት የመፍጠር አደጋን ይጋብዛሉ፡፡ በረዥም ዘመን ነባር ቡድኖች ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው የማካተት ፖሊሲዎች፣ ለምሣሌ ብዙሃኑ የሚናገረውን ቋንቋ መያዝ፣ በአንዳንድ ቡድኖች፣ በተለይ በስደት በመጡ ቡድኖች ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡ የአፋኝ ፖሊሲ ኢላማ የሆነ ቡድን፣ የመነጠል ስሜት

ከበረታበትና የሰላማዊ መፍትሔ ዕድል ጠብቦ ከታየው፣ ወደ አመጽ ሊዞር ይችላል፡፡

## ብዙሀነትን መቀበል

የአንድነት ፈተና የተጋረጠባቸው ዴሞክራሲያዊ አገሮች፣ ፌዴሬሽኖች ጭምር፣ በመቻቻልና በመፈቃቀድ ድባብ ውስጥ፣ አዎንታዊ አገራዊ የፖለቲካ ማንነትን ሊያጠናክሩ ይችላሉ - ዜጎች ግምት ከሚሰጧቸው ሌሎች ማንነቶች ጋር የተጣጣመ ስሜት የሚፈጥር፡፡ ብዙሀነትን እንደ አገራዊ እሴት መያዝ፣ አንድነትን ሊያጎለብት ይችላል፡፡

የአንድ ዴሞክራሲያዊ አገር አንድነት ዘላቂ እንዲሆን፣ እጅግ የሚበዛው የሀገሪቱ ዜጋ የአገራዊ ማንነት መንፈስ እና ከአገሪቱ ጋር የመቆራኘት ስሜት መያዝ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ በእጅጉ አጠራጣሪ የሚሆነው፣ አንድ ጉልህ ቡድን፣ በብርቱ ስሜት የያዘው የአካባቢ፣ የብሔረሰብ፣ የሃይማኖት ወይም የቋንቋ ማንነት፣ ከአገራዊ ማንነት ጋር ይጋጫል ብሎ ሲያምን ነው - ለምሣሌ፣ ህዝቡ በመንግስቱ ውስጥ በእጅጉ የሥልጣን ውክልና ካጠረው፣ ሃይማኖቱ አድሎ ከተፈፀመበት ወይም ቋንቋው ባለመከበሩ አሊያም በቋንቋው እንዲጠቀም ያልተፈቀደለት በመሆኑ፡፡

ብዙውን ጊዜ፣ የአንድነት ፈተና፣ የአናሳ ቡድኖችን ጥያቄ መመለስን ብቻ ሳይሆን፣ በአናሳና በብዙሀን ማህበረሰቦች ውስጥ የመቻቻልና የመፈቃቀድ ፖለቲካዊ ባህል ማዳበርንም ጭምር ይጠይቃል፡፡ አንዳንድ ብዙሃኖች፣ አገራቸውን የሚስሉት ራሳቸውን በሚያንፀባርቁ ገፅታዎች ነው - አናሣ ማህበረሰቦችን ሳያቅፍ፡፡ ይበልጥ አዎንታዊ የሆነ ባህል፣ ቢያንስ ቢያንስ የልዩነቶች መቻቻልና መፈቃቀድን ያበረታታል፡፡ ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው ደግሞ፣ ብዙሀነትን እንደ አንድ አገራዊ ባህርይ የመቀበል የጋራ መግባባት ሲኖር ነው፣ ከተለያዩ የህብረተሰቡ አዝማሚያዎች ጋር የሚጣጣሙ ፖሊሲዎችና ትእምርቶች ጋር፡፡ ህንድ፣ ናይጀሪያ፣

ኢትዮጵያ፣ ካናዳ፣ ስዊዘርላንድ እና ደቡብ አፍሪካ፤ ብዙሀነትን በማቀፍ አንድነትን የማጠናከር አካሄድ የሚከተሉ ፌዴሬሽኖች ምሳሌ ናቸው።

በተለያዩ ማህበረሰቦች አናሳና ብዙሃን ውስጥ ያሉ ፖለቲከኞች ወይም መሪዎች፤ በቡድኖች መካከል ጠንካራ ፀበኛ ስሜትና ፍርሃት ለማራገብ የሚሞክሩ ከሆነ፤ ብዙሀነትን የሚያቅፍ ባህል ለማዳበር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። የገነነ አብላጫ የያዘ ቡድን፤ ለምሳሌ አንድ የሃይማኖት ወይም የቋንቋ ቡድን፤ ታሪካዊ ጥቅሞቹን ለመተው ፈቃደኝነቱ ሊጐድለው ይችላል። ዩጎዝላቪያ አሳዛኝ ምሳሌ ነች። የማንዴላ፣ የጋንዲ እና የኔህሩ አብነቶች እንደሚያሳዩት፤ አዎንታዊ አመራር ወሳኝ ሊሆን ይችላል።

## ሚዛናዊ አካሄድ፤ ብዙሀነትን በተመለከተ

ብዙሀነትን የማቀፍ ባህል፤ የ‹‹ዳር-ገንቢ›› እና የ«ውስጥ-ገንቢ» ሚዛናዊ አካሄድን ይጠይቃል። ‹‹ዳር-ገንቢ›› የሚባለው አካሄድ፤ ክልላዊ መንግስት ለመፍጠር የሚቀርቡት ጥያቄዎችን ማስተናገድን ይተገብራል። «ውስጥ-ገንቢ» ደግሞ፤ ዋና ዋና አናሳዎች ወደ ፌዴራሉ መንግስት ትእምርቶች፣ ተቋማትና ፖሊሲዎች፤ እንዲሁም በሌሎች ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎች የተካተቱ እንዲሆኑ ማረጋገጥን ይመለከታል።

የአካባቢው ህዝብ የሚቆጣጠራቸው ክልላዊ መንግስታትን የመፍጠርና የማጠናከር አካሄድ፤ የየክልሉ ህዝብ ለራሱ የሚፈይዱለት ውሳኔዎችን እንዲወስን የሥልጣን ባለቤት ሊያደርገው ይችላል። ህዝቦቹ፤ የየራሳቸው ልዩ ባህርይ በየአካባቢው በሚገኙ መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ ተንፀባርቆ እንዲያዩም ይፈቅዳል። እነዚህ የፌዴራላዊ መፈቃቀድና የፌዴራላዊ ባህል ዋነኛ ባህርያት ሲሆኑ፤ አገራዊና ክልላዊ የፖለቲካ ማህበረሰቦች በጋራ ተጣጥመው እንዲኖሩ የሚፈቅዱ ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ዋና ዋና ክልላዊ አናሳዎች በፌዴራሉ

መንግስት ተቋማት ውስጥ ማቀፍን የዘነጋ፤ የፌዴራሉ አባል መንግስታትን ሥልጣን የማጠናከር ፖሊሲ፤ በሀገሪቱ ውስጥ የመበታተን እንቅስቃሴን የማፋጠን አደጋን ይጋብዛል፡፡ የራሳቸው የማንነት ስሜት የያዙ ዋና ዋና ቡድኖች፤ በፌዴራሉ ተቋማት ውስጥ በአግባቡ መንፀባረቃቸውን ካላዩ፤ የአገራዊ ማንነት ስሜታቸውን ጠብቀው የሚዘልቁበት ወይም የሚያሳድጉበት እድል ጠባብ ነው፤ በተቃራኒው ደግሞ በማያቋርጥ ሁኔታ ይበልጥ ያለመማከልን ወይም መገንጠልን የሚደግፉበት እድል ሰፊ ነው፡፡

## «ዳር-ገንቢ» - አለመማከል

«ዳር-ገንቢ» የተሰኘው አካሄድ፤ የአሰፋፈር ክምችት ካለው ህዝብ ለሚመጡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ሲባል፤ ክልላዊ መንግሥታት እንዲፈጠሩ ወይም ሥልጣናቸው እንዲጠናከር ማድረግን የሚመለከት ሲሆን፤ የፌዴራላዊ አሰራር ሁነኛ መለያ ባህርይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፤ ተጨባጭ ጥያቄዎች አሉ፡፡ በነባር ፌዴሬሽን ውስጥ አዳዲስ ክልላዊ መንግሥታትን መፍጠር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ክልላዊ ድንበሮች፤ አንድ ወጥ የሆነ ህዝብ ብቻ የሚይዙበት አጋጣሚም ብርቅ ነው፤ እናም በክልሎች ውስጥ ጉልህ አናሳዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስንት ክልሎችን መፍጠር ይቻላል የሚለው ጥያቄ በተጨባጭ ሲታይ፤ የቁጥር ገደብ ሊኖር ይችላል፡፡ ጠንካራ የተለየ ማንነት ስሜት ያላቸው አንዳንድ ህዝቦች፤ አሰፋፈራቸው የተበታተነ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ በጣሙን ያልተመጣጠነ አሰራሮች እንዲዘልቁ ማድረግም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡

በበርካታ ፌዴሬሽኖች፤ በተለይም እጅግ ብዙሀነትን የያዙ እንደ ህንድ፣ ካናዳ እና ስዊዘርላንድ በመሳሰሉት፤ የአገር መረጋጋት ጉዳይ ተመርኩዞ የቆየው፤ በመንግስቶቻቸው ያልተማከለ ፌዴራላዊ ቅርፅ ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፤ ፌዴሬሽኑ አንድ ጊዜ ቅርፁን ከያዘ በኋላ፤ ህገመንግስታዊ ስነስርአቶች፤ አዳዲስ የፌዴራል አባላትን ለመፍጠር ድንበር መከለስን አስቸጋሪ ያደርጉታል፡፡ ህንድ

በዚህ በማፈንገጥ ተለይታ የምትጠቀስ ነች፣ የግዛቶቿን ካርታ ከልሳለች፣ በየጊዜውም አዳዲስ ግዛቶችን ፈጥራለች፡፡ ስዊዘርላንድ፣ ከዝርዝር የሪፈረንደም ስነስርአታዊ ሂደት በኋላ፣ አዲሱን የጁራ ክልል ፈጥራለች፡፡ የናይጀሪያ የግዛት ድንበሮች፣ ከፍተኛ ለውጥ በሚያስከትል ሁኔታ በወታደራዊ አገዛዞች ተከልሰዋል - ህገመንግስታዊ ያልሆኑ አግባቦችን በመጠቀም፡፡

እንዲሁም፣ እንደ ህንድ፣ ናይጀሪያና ኢትዮጵያ ያሉ አንዳንድ ፌዴሬሽኖች፣ ከፌዴራሉ አባል ክልሎች ቁጥር በእጅጉ የሚበልጡ የቋንቋ ቡድኖችና ብሔረሰቦች አሏቸው፡፡ ሁሉም አነስተኛ ቡድኖች፣ የየራሳቸው ክልላዊ መንግሥት ሊኖራቸው ይችላል ብሎ ማሰብ ከተግባራዊነት ጋር አይጣጣምም በእርግጥ በአንዳንድ የህንድ ግዛቶች በክልላዊ መንግሥታት ውስጥ ንኡስ መንግሥታት አሏቸው - የአብላጫ ሕዝብ ባለባቸው ክልላዊ መንግሥታት ውስጥ በተጨማሪም፣ ህዝቦች በማስመሪያ ተለክተው በተበጁ መልከዓምድራዊ ስፍራዎች ውስጥ የሚኖሩ አይደሉም፡፡ እናም አንድ ክልላዊ መንግስት፣ አንድን ህዝብ ሙሉ ለሙሉ አጠቃልሎ ላይዝ ይችላል፣ በአብዛኛው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጉልህ አናሳዎችም ይኖሩታል፡፡ በመጨረሻም፣ ተለይተው የሚታወቁ የብሔረሰብ፣ የቋንቋ ወይም የሀይማኖት ቡድኖች፣ በሰፊው የተሰራጩ በሚሆኑበት ጊዜ፣ በአንድ ክልል ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር የሚይዙበት እድል አይኖርም፡፡ ስለሆነም፣ የክልላዊ መንግሥታት መፈጠር፣ ብዙሀነትን በተመለከተ ከሚሰጡ ምላሾች መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል፣ ግን የተሟላ ምላሽ ሊሆን አይችልም፡፡

በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ አንድ የፌደሬሽኑ አካል ከሌሎች ይልቅ፣ በእጅጉ አለመማከልን የሚደግፍ ይሆናል፡፡ ይህም ያልተመጣጠኑ አሰራሮችን የመፈተሽና የመፍጠር ጉዳይን ያስነሳል፡፡ ይሁንእንጂ፣ እነዚህ ያልተመጣጠኑ አሰራሮች፣ በክልሎች ህገመንግስታዊ ስልጣኖች ላይ ጉልህ ልዩነቶችን የሚያስከትሉ ከሆኑ፣ በቀጣይነት ለማዝለቅ አስቸጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ - በተለይ ተጨማሪ ስልጣኖችን የሚያገኘው ክልል በንፅፅር ትልቅ ከሆነ፡፡

## ውስጥ-ገንቢ፤ ሁሉን ወካይ ማዕከል

ውስጥ-ገንቢ የተሰኘው አካሄድ፤ በፌዴራሉ መንግስት ተቋማት ውስጥ፤ ዋና ዋና ህዝቦች የሚያገኙትን ዕውቅናና ሚናቸውን በማጎልበት፤ እንዲሁም ለአናሳዎች ጥበቃ በመስጠት አንድነትን ያጠናክራል።

የአንድነት ፈተናን በተመለከተ የሚኖር ሚዛናዊ አካሄድ በአብዛኛው፤ የተለየ ማንነት የያዙ ዋና ዋና ህዝቦች፤ በፌዴራሉ ተቋማትና በጠቅላላው ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎች ውስጥ በአግባቡ ዕውቅናና ውክልና አግኝተናል የሚል ስሜት መያዛቸውን ለማረጋገጥ፤ የውስጥ-ገንቢ እርምጃዎችን ያካትታል።

ሚዛናዊ አካሄድ፤ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል።

- የአገሪቱን ወይም የአገራዊ ማህበረሰቡን መገለጫ፤ አገራዊ ተቀባይነት ያገኙ ትእምርቶችን (መብቶችን፣ ሰንደቅ ዓላማን፤ ወዘተ)፤ እንዲሁም የዋና ዋና ህዝቦች ትእምርቶችን፤ ታሪክን፣ ሃይማኖትንና ቋንቋን በአግባቡ ያካተተ እንዲሆን ማድረግ (የሀገሪቱን መገለጫ፤ አብላጫ ያለውን ህዝብ በሚጠቅስ አኳኋን ብቻ አለማድረግ)
- በአንድነት እንደሚያሰባስቡ፤ የጋራ ጥቅምን እንደሚያስገኙ በሰፊው የሚታመንባቸው አገራዊ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን ማጠናከር (ለምሣሌ የጋራ ገበያ፣ አገራዊ የጤናና የጡረታ ስርዓቶችን
- ዋና ዋና ህዝቦች በፌዴራሉ ተቋማት ውስጥ በአግባቡ መወከላቸውንና ሥልጣን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ - መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ አሰራሮች፤ በመንግስት፣ በሲቪል ሰርቪስ፣ በወታደራዊ ተቋማት ውስጥ ሁሉንም የሚወክል ጥንቅርን ሊያረጋግጡ ይችላሉ። ወደ ፅንፍ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ለምሣሌ፣ ድህረ-ግጭት ሁኔታ ውስጥ፤ በዋና ዋና ማህበረሰቦች መካከል በድርድር የመጣ፤ በመንግስት ውስጥ ስልጣን የመጋራት ስምምነት ሊኖር ይችላል።

- በፌዴራሉ አባል ክልሎች ውስጥ ላሉ አናሳዎች ጥበቃ መስጠት፡፡ ፌዴሬሽኖች ብዙ ጊዜ፣ በአገራዊና ክልላዊ መዋቅሮች ላይ፣ በየፊናቸው የተለያዩ አብላጫና አናሳ ቡድኖች አሏቸው፡፡ በክልሎች ውስጥ ለአናሳዎች የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የትምህርት መብቶች፣ የሲቪል ሰርቪስ ወዘተ ጥበቃ መስጠት፣ በአጠቃላይ በፌደሬሽኑ ውስጥ የሚኖረው፣ የመብትና የጥበቃ ሚዛን አካል ሊሆን ይችላል፡፡

የቋንቋ ፖሊሲ ብዙውን ጊዜ፣ በጣም ጥንቃቄን የሚሻ ነው፡፡ የተለያዩ ቋንቋዎች በሚነገሩባቸው አገራት ውስጥ ከፌዴራሊዝም ትልልቅ ጠቀሜታዎች አንዱ፣ የተለያዩ ቋንቋዎች በተለያዩ አካባቢዎች አብላጫ እንዲሆኑ መፍቀዱ ነው (በዳር-ገንቢነት)፡፡ ነገር ግን፣ በአገራዊና በክልል ደረጃ፣ ለአናሳዎች የቋንቋ ጥያቄ ምላሽ መስጠት አለበት (በውስጥ-ገንቢነት)፡፡ በተግባር ሲታይ ብዙውን ጊዜ፣ የቋንቋ ፖሊሲ እጅግ ውስብስብ ጉዳይ ነው - ብዙ ልዩ አሰራሮችን የያዘ፡፡ በአንዳንድ ፌዴሬሽኖች (በህንድ፣ ናይጀሪያ፣ ማሌዢያ፣ ኢትዮጵያ) ለአካባቢያዊ ቋንቋዎች ዕውቅና ከመስጠት በተጨማሪ፣ በአካባቢው ነባር ያልሆነ ቋንቋ ይበልጥ እንደ ገለልተኛ በመታየቱ ምክንያት፣ እንደ ዋና አገናኝ ቋንቋ ሊመረጥ ይችላል፣ (እንግሊዝኛ ደግሞ፣ በዋና አለም አቀፍ ቋንቋነቱም ጥቅም አለው)፡፡ ፓኪስታን፣ በጣም አናሣ የሆነ ህዝብ የሚናገረውን ‹‹ኡርዱ››የተሰኘ ቋንቋ የሥራ ቋንቋ አድርጋለች - የእንግሊዝኛ እና ፑንጃቢ ቋንቋዎች በጣም ፋይዳ ያላቸው ሆነው ቢቀጥሉም፡፡ ፌዴሬሽን ያልሆነችው ኢንዶኔዢያም፣ የአናሳ ቋንቋን የአገሪቱ የስራ ቋንቋ አድርጋለች - ኢንዶኔዢያኛ፡፡

አብላጫ የያዙ ህዝቦች፣ ለአናሳ ቋንቋዎች እውቅና የመስጠት አሰራር ላይ ቅሬታ ሊኖራቸው ይችላል፣ አናሳዎች ለእውቅና የሚጎተጉቱትን ያህል፡፡ እያንዳንዱ ሀገር፣ የራሱን የተመዛዘነ ሁኔታ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ብዙውን ጊዜ (ለምሳሌ በካናዳ፣ በህንድ፣ በስትዊዘርላንድ፣ በኢትዮጵያ እንደተደረገው ሁሉ) አንዳንድ የቋንቋ መብቶች፣ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ፣ በፌዴራሉ

ህገመንግስት ውስጥ ጥበቃ አግኝተዋል፡፡ በሌሎች ሀገሮች ውስጥ ደግሞ፤ እነኚህ መብቶች በዋናነት የህግ ወይም የአሰራር ጉዳይ እንዲሆኑ ተደርገው፤ ለእያንዳንዱ የመንግስት መዋቅር የተተው ይሆናሉ፡፡ ለቋንቋ ፖሊሲ መሠረት የሚሆነው ፍልስፍና፤ ከፌዴሬሽን ፌዴሬሽን ይለያያል፡፡ አንዳንዶቹ ፌዴሬሽኖች በየትኛውም ቦታ ቢሆን ለግለሰቦች መብቶች ጉልህ ትኩረት ይሰጣሉ፤ ሌሎች ደግሞ የቋንቋ መብትን ከቦታ (ከመንግስት መዋቅሮች) ጋር ያስተሳስሩታል፡፡

**የቋንቋ ፖሊሲ ገጽታዎች፤ በአንዳንድ ፌዴሬሽኖች**

ህንድ፤ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሰዎች የሚናገሯቸው 40 ቋንቋዎች አሏት፡፡ የ18 በመቶ ህንዳውያን የእፍ መፍቻ የሆነውና ከ40 በመቶ በላይ ህንዳውያን የሚናገሩት ሂንዲ ቋንቋ፤ ዋነኛው አገር በቀል ቋንቋ ነው፤ እንግሊዝኛም እንደ መግባቢያ ቋንቋ ፋይዳ አለው፡፡ የህንድ ግዛቶች፤ በህገመንግስት ከተዘረዘሩት የህንድ ቋንቋዎች መካከል የትኞቹን በኦፊሴልነት እንደሚጠቀሙ መምረጥ ይችላሉ፤ በኦፊሴላዊ ቋንቋ ወይም በሌሎች ቋንቋዎች አገልግሎት መስጠትም ይችላሉ፡፡ ናይጀሪያ፤ ሰፊ አገልግሎት የሚሰጡ ሦስት አገር በቀል ኦፊሴላዊ ቋንቋዎች አሏት፤ ግን ቢያንስ ሌሎች 450 ቋንቋዎችም አሏት፡፡ እንግሊዝኛ ዋነኛው የመንግስት አስተዳደርና የትምህርት ቋንቋ ነው፤ በእርግጥ ሌሎች አካባቢያዊ ቋንቋዎችንም መጠቀም ይቻላል፤ አንዳንድ የዜጎች መብቶች፤ (ለምሣሌ የፍ/ቤት የቋንቋ አጠቃቀም ላይ)፤ በዜጎች ምርጫ የሚወሰኑ ሳይሆኑ፤ ‹‹ያግባባል ወይ?›› በሚለው ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ፤ ሁለት ዋና ዋና አገር በቀል ቋንቋዎች፤ አስራ አንድ እነስ ያሉና በርካታ በብሔረሰብ ደረጃ የሚነገሩ ቋንቋዎች አሏት*፡፡ በኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ቋንቋ የለም፤ በመርህ ደረጃ ሁሉም ቋንቋዎች እኩል እውቅና አግኝተዋል፡፡ እንግሊዝኛም በትምህርትና በመንግስት መስሪያ ቤቶች ግልጋሎት ይሰጣል፡፡ አማርኛ የፌዴራል መንግስቱ እና የአንዳንድ ክልሎች የሥራ ቋንቋ ነው፤ እያንዳንዱ ክልል የራሱን የሥራ ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች ይመርጣል፡፡ ደቡብ አፍሪካ፤ ሁለት አውሮፓዊ ቋንቋዎችና ዘጠኝ ጉልህ አገር በቀል ቋንቋዎች ሲኖሯት፤ ከእነዚህም ውስጥ የህዝቡን ሩብ የሚበልጥ ተናጋሪ ያለው የለም፡፡ እንግሊዝኛ ገናናው ቋንቋ ነው፤ አገር በቀል ቋንቋዎች በአንዳንድ የትምህርት እና የአካባቢ መስተዳድር ተቋማት ውስጥ የንግግር ቋንቋ

